የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

**Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP)**

የካቲት15 1998 ዓም

## መልዕክተ ኢሕአፓ

### የወያኔን ህግ መጣስ ህጋዊ ግዴታ ነው

ገና ከጥንስሱ ከህግና ከሀገር ጥቅም ጋር ተጣልቶ፥ በውንብድናና በሀገር ግንጠላ ጎዳና የነጎደው ወያኔ፥ ዛሬ ጊዜ የሰጠው ቅል እንዲሉ ለቤተ መንግሥትና ለሥልጣን ስለበቃ፥ በብጤዎቹ ያስረቀቀውንና ያፀደቀውን "ህገ ወያኔ" ህገ መንግሥት ብሎ ሰይሞ፥ ተቀበሉልኝ እያለ ነው:: ይህ አንቀፅ 39ን ሌሎችንም የይስሙላ መብት አዋቂ ግን ከሞላ ጎደል የገዢውን ቡድን ጠባብ ጥቅም አስጠባቂ አንቀፆችን ያቀፈ ሰነድ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ህግ መንግሥት ተብሎ ሊወሰድና ሊከበር የሚችልበት መንገድ ሊኖር እንደማይችል አከራካሪ አይደለም::

የመለስ ቡድን ህገ መንግሥቴን ተቀበሉ ብሎ መለፈፉ የሚጠበቅ ነው:: የበላይነቴን እመኑ ማለቱ ነው:: የምርጫ ህጌን ተቀበሉ፤ የምርጫ ቦርዴን ተቀበሉ ሲል የነበረውም ያው የሕዝብን ድምፅ ለማፈን ብሎ እንደነበረ በመርጫው ሲሸነፍ አሻፈረኝ ብሎ በመቀጠሉ ዳግም በገሀድ እያየነው ያለ ነው:: ህግ መንግሥት የሚለውንም በግድ ተቀበሉ ሲል፥ በዚህ ሰነዱ ያሰፈረውን ህገወጥ አንቀፅ ሁሉ ሰጥ ለጥ ብለን እንድንቀበል ነው:: ወያኔ ህግ ሲል ህግን መብትን እየጣሰ ነውና የእርሱን ህግ መቀበል ማለት ጭቆናና መብት ገፈፋን መቀበል ይሆናል:: የመለስን ህገ መንግሥት ተብዬ የማንቀበልበት ምክንያት ብዙ ነው::

በቅድሚያ በዚህ ሰነድ ላይ ህዝብ በነፃ ተወያይቶና አርሞ በነፃ በፍላጎቱ ያፀደቀው አይደለም:: ሰነዱ ልክ እንደ ወያኔ በሕዝብ ላይ የተጫነ ነው-- ህዝብን አይወክልም:: ወያኔ ራሱም ህገ ወጥ አገዛዝ በመሆኑ፥ ሰነዱ ህጋዊነት ሊኖረው አይችልም:: ይህ ሀቅ ትላንት አከራካሪ ነው ከተባለም ዛሬ ግን የመለስ ጭፍራ በምርጫ ተሸንፎ ግን አፄ በጉልበቱ ነኝ ብሎ ሲሰየም ህግ ወጥነቱን ለሁሉም አሳይቷል:: ስለዚህም ሥልጣን ለቆ መሰወር የሚገባው ቡድን እምቢኝ ብሎ በጉልበቱ ሲቀጥል ህጌን አክብሩ ሲል፥ አዎ እንቀበለዋለን ብሎ መፈጠሙ ከስህተት በላይ ነው:: በተጨማሪ ሕዝብ እንኳን ተሰብስቦ፤ መክሮ፤

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
USA
Tel: (202)-291-4217
Fax: (202)-291-7645
E-mail: ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
FRANCE

Website: http://www.EPRP.com

EPRP
Postbus 1253
1000 BG Amsterdam
HOLLAND

አሻሽሎ ያፀደቀውንም ህገ መንግሥትም ቢሆን፥ ዜጎች አልቀበለውም ብለው የመቃወም መብታቸው የተጠበቀ ነው። ጤነኛና ህዝባዊ ህገ መንግሥት በቅድሚያ የሕዝብን የመቃወም መብት ማክበር አለበት። ህጋዊና ሰላማዊ ትግል የሚቻል እስከሆነ ድረስ ተቃውሞዎች በሰላማዊ መልክ ይካሄዱ ማለት ተገቢ ቢሆንም፥ ህግ መንግሥትን አትቃወሙ ማለት ግን ዴሞክራሲያዊ አይደለም። ዴሞክራሲ የብዙሀንን መብት ብቻ ማክበር ሳይሆን፥ በተለይም የህዳጣንን የግለሰቦችንም መብት ማክበር ይጠበቅበታል። ስለዚህም ሚሊዮኖች ያፀደቁትን ሺዎች የመቃወም መብታቸው  ሁሌም መከበር አለበት። በዚህም የተነሳ ማንም ኃይል የህዝብን የመቃወም መብት ከቶም ሊገድብ አይችልም።

ተደጋግሞ እንደተነገረው የመለስ ዜናዊ መሰሪ ቡድን በአፈ ጮሌነት በሚቀደው ቦይ በእሺታ መፍሰስ ቢያንስ ከተቃዋሚዎች አይጠበቅም። ወያኔ የእኔን ህግ አለመቀበል ህገ-ወጥነት ነው ሲል፥ እኛ መቸ አንቀበልም አልን፣ ህገ መንግሥት ያልከውን እንቀበላላን ብለው ተቃዋሚዎች ሊነጠፉለት አይገባም። የትግል ዕቅዳችንን፣ መፈክራችንን ሆነ ግባችንን ወሳኝ አሸባሪው አገዛዝ ሊሆን አይችልም። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔን መንግሥት ማለቱ ራሱ ተገቢ አይደለም። በግድ የሚገዛ ኃይል ነው። በጉልበት። በጭፍጨፋ። ለዚህ ነው አገዛዝ የምንለው። ለመለስ ዜናዊም አንቱታን የማንለግሰውም ያለምክንያት አለመሆኑ መታወቅ አለበት። መንግሥት ስንል፥ በህዝብ ድምፅ ተሰይሞ የሚገኘውን ከመሆኑ በላይ በፅንሰ ሀሳብም ደረጃ ቢሆን፥ ከተወሰነ ድርጅት ውጪ ቀጣይነትን ባንፀባረቀ መልክ ያለውን ሥርዓት ነው። አንዳንድ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከዚህ ቀደም የወያኔን የምርጫ ህግና ቦርድ በመቃወምና አንቀበልም እምቢ፥ አሻፈረን በማለታቸው፥ የተከተለው ጉዳት የሚታወቅ ነው። ለወያኔም ለባዕዳንም እምቢ አንቀበልም ማለት ኢትዮጵያዊ ጠባይ መሆን አለበት ስንል ውሎ አድሯል። የአሜሪካ ኤምባሲ ወይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ባልሥልጣኖች ይህ ይሁን ሲሉ አሜን ብሎ መቀበሉ አሳፋሪ እንጂ አኩሪ አይደለም። ሁሌም የኢትዮጵያን ጠቅም ማስቀደም ያስፈልጋል።

የመለስ ቡድን ከዚህ የተፃረረ ነው። ታሪኩ ሁሉ ሀገርን ጎድቶ ለባዕድ መጎንበስ ነው። በሱዳን ትዕዛዝ የተከዜን ድልድይ ሊያፈርስ ሞክሯል። በሱዳን ትዕዛዝ የሀገርን ዛፍና ጫካ በሱዳን አስመንጥሯል። በአሜሪካና ሱዳን ትዕዛዝ ለረሃብ የተጋለጠውን የትግራይ ህዝብ ወደ ሱዳን ለማጋዝ ሞክሮ በወዲ ከውሊና ሌሎችም ጣቢያዎች በሺዎች ለሞት ዳርጎ የገንዘብ ትርፍ አግኝቷል። ለሊቢያው መሪ ጋዳፊ አረብ ነኝ፣ ኢትዮጵያውያን አረብ ናቸው ብሎ መለስ ቀጥፎ እርዳታ አግኝቷል። የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን ለሱዳን መንግሥት አሳልፎ በመስጠት በብዛት ለሞት ዳርጓል። የትግራይ ሴቶችን ለሱዳን ባለሥልጣኖች፣ ስደተኞችን ለበዝባዥ ባለእርሻዎች አሳልፎ ሰጥቶ ለራሱ ትርፍ አግብቷል። የመለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ግፍና ወንጀል ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም ብንል ማጋነን አይሆንም። የመለስ ቡድን የሕውዜንን ዕልቂት ራሱ መገፋፋቱም በውስጠ አዋቂዎች የተጋለጠ ጉዳይ ነው። መለስ ዜናዊ ለባዕዳን በተለይም ለእንግሊዝና ለአሜሪካ ጭፍን ሎሌ ሆኖ መክረሙ ደግሞ ለማንም

ምስጢር አይደለም፡፡ ታዲያ ለዚህ ዓይነቱ ሀገርን የካደ ቡድን ለሚያወጣው ህግ ተገዢ ነን ብሎ መጮሁ ያሳዝናል ብንል ምን ስህተት አለው?

በህዝብ ላይ በባዕዳን ሻጥርና ድጋፍ የተጫነን ቡድን ህገ ወጥ ማለቱ መክበድ ባልነበረበት ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ግን ፖለቲካው ጨልሞባቸው፤ ተምታቶባቸው ተቃውሞ ሲያሰሙ ከመለስ ቡድን በተለየ አልሆን ብሏል፡፡ ፀረ ሰላም የአመፅ ኃይሎች ሲሉም ማድመጥ ተገደናል፡፡ ቆራጥና ፅኑ እምቢታ ጋር ይጣላሉ፡፡ ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆን ይሽቀዳደማሉ፡፡ ጠላት ወዳጅ ሳይሆን ጎንበስ ብለውና ወኔን አጥፍተው “አለና” ለማለት ይቾኩላሉ፡፡ ተቀዋሚ ኃይሎች የወያኔን ህገ መንግሥት ተብዬ ሰነድ አንቀበለውም የማለቱ ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እምቢ ማለቱ መብታቸው ነው ማለቱ ትክክል ነው፡፡ ለባዕዳንም ቢሆን ይህ መብት በሀገራቸውም ያለ መሆኑ ሊጠቀሙላቸው ይገባል፡፡ የወያኔን ህገ መንግሥት ተቀብለንና አክብረን እንታገላለን ማለቱ ግን እውነቱ ይነገር ከተባለ፥ አንታገልም ከማለት ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ በወያኔ ዕዝ መሠረት መታገል የሚበጅ አይደለምና ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ ግልፅ ካልሆነ፥ በትግሉ ወደፊት ለመግፋት የሚከብድ ይሆናል፡፡ ስለዚህም የመለስን ህገ መንግሥት እንቀበላለን ማለቱ በጊዜ መቆም አለበት፡፡ ህገ ምርጫውንና ቦርዱን እንቀበላላን ከማለቱ ያላነስ ጉዳት ያስከትላል፡፡ የተለጣፊዎችም አቋም ነው እውነቱ ይነገር ከተባለ ፡፡

የመለስ ዜናዊ ህግ መንግሥት የወያኔ ሰነድ ነው፡፡ ህዝብን አይወክልም፤ የኢትዮጵያም አይደለም፡፡ እንቀበለዋለን እንገዛበተለን የሚሉ ወያኔዎችና ተለጣፊዎቹ ብቻ መሆን አለባቸው፡፡ ባዕዳንን ባማዳመጥ ብቻ አሳፋሪ አቋም ማስተጋበቱም ማቆም አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይል በቅድሚያና በመጀመሪያ ማዳመጥ ያለበት መሰሪውን መለስ ወይም ባዕዳንን ሳይሆን፥ የኢትዮጵያን ህዝብ መሆን አለበት፡፡